የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ግንቦት ቅጽ 1 ቁጥር 11


## በ90 ቀናት ውስጥ 10 ቢሊዮን ብር የሚሰባሰብበት ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ

ፕሮጀክቱ ይፋ የተደረገው ግንቦት 11 ቀን 2015 ዓ.ም በፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ስፖርት ኦፐሬሽን ክፍል አስተባባሪነት በመሰብሰቢያ አዳራሹ ከረፋዱ 3:30 ጀምሮ በተካሔደው የኩባንያው ወርኀዊ የሠራተኞች ጉባኤ ላይ ነው፡፡

በሠራተኞች መካከል ይበልጥ መቀራረብን መፍጠርና ሁሉም የኩባንያው ሠራተኞች ያላቸውን አቅምና ተሰጥዖ በማውጣት በፍጹም የእኔነት ስሜትና ነጻነት ሥራቸውን እንዲከውኑ ማስቻልን ዋና ዓላማው አድርጎ በተካሔደው መርሐ ግብር ላይ የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ፣ የየክፍላቱ ቺፍ ኃላፊዎች፣ ዳይሬክተሮች፣ እንዲሁም የኩባንያው አጠቃላይ ሠራተኞች ተሳትፈዋል፡፡

በኅሊና ጸሎት የተጀመረው ይህ መሰናዶ ከተለመደው አዘገጃጀት በተለየ አዝናኝ ፕሮግራሞችን አካትቶ የተካሔደ ሲሆን የኩባንያው መዝሙር ተዘምሮ ከዚያም በማስቀጠል የግጥም ዝግጅት ቀርቧል፡፡ በመቀጠልም በኩባንያው ያሉ ሁለት አዳዲስ ጉዳዮችን በተመለከተ ማብራሪያ የሰጡት የፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ በቀዳሚነት በሚቀጥሉት 90 ቀናት ውስጥ በቲኤስኤም ተነሣሽነት ሥር 10 ቢሊዮን ብር ካፒታል የማሰባሰብ ልዩ መርሐግብር መነደፉን ይፋ አድርገው ለፕሮጀክቱ እውን መሆን እያንዳንዱ የኩባንያው ሠራተኛ በነፍስ ወከፍ 10 ሚሊዮን ብር አክሲዮን መሸጥ እንደሚገባው እና ለመርሐግብሩ ስኬት አስፈላጊው ስልጠና እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

ምስል በኑበዩ ዳንኤል



> “ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ኩባንያው ሊደርስ ያሰባቸውን ግቦች በተመለከተ እያንዳንዱ ሠራተኛ ግንዛቤ እንዲኖረው እንደሚያስፈልግ አሳስበው ተቋሙ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ቀደም ሲል ከሚመራባቸው ዋና ዋና ግቦች በተጨማሪነት የሚካተቱ ሌሎች ግቦችንም በሁለተኛ አዲስ ጉዳይነት አቅርበዋል፡፡

ኩባንያችን ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ካነገበው ታላቅ ራዕይ አንጻር የሚገጥሙን ፈተናዎች ቀላል እንዳልሆኑ፣ የምንጓዝበት መንገድም አልጋ በአልጋ እንደማይሆን እሙን መሆኑን የተናገሩት ዋና ሥራ አስፋጻሚው የሚገጥሙን እንቅፋቶች የያዝነውን እንድንጥልና ተስፋ እንድንቆርጥ የሚገፋፉ በመሆናቸው ታላቁን ትልማችንን እውን እንዳናደርግ ጋሬጣ ቢሆኑብንም በተባበረ ክንድ፣ በእውነተኛ ቤተሰባዊነት፣ በአስደናቂ የሥራ ባሕል ተግተን ፈተናዎቻችንን ማለፋችን ውጥናችንንም እውን ማድረጋችን የማይቀር መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በዕለቱም የግጥም ዝግጅት፣ ጭፈራ፣ ሙዚቃ፣ የተለያዩ ሠራተኞችን የሚያሳትፉ አዝናኝ ፕሮግራሞች የቀረቡ ሲሆን በመጨረሻም የፐርፐዝብላክ ኬርስ ፋውንዴሽንን ለመደገፍ በተካሔደ ጨረታ 200 ሺህ ብር ገቢ ማድረግ ተችሎ የመርሐግብሩ ፍጻሜ ሆኗል፡፡

## የፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ትሬዲንግ አክሲዮን ማኅበር የ 2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ቀረበ፡፡

የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የዘጠኝ ወራት አጠቃላይ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መቅረቡን የኩባንያው ፕላኒንግ ዩኒት ማናጀር አቶ ሳምሶን በቀለ አስታውቀዋል፡፡

በሪፖርቱ ላይ የፐርፐዝ ብላክን የስራ ክፍሎች ጨምሮ የተሰማራባቸው ዘርፎች አጠቃላይ አፈጻጸም በዝርዝር የቀረበ ሲሆን እንደተመዘገቡት ስኬቶች ሁሉ በርካታ ክፍተቶች መስተዋላቸው ተጠቁሟል፡፡

Purpose Black ETHIOPIA

ሥራዎችን በሰለጠነ እና ብቃት ባለው የሰው ኃይል በመታገዝ የማከናወን ተግባር ከምን ጊዜም በላይ በመጠናከሩ የድርጅቱን ሃብት ከብክነት ለመታደግ ተችሏል ያሉት ኃላፊው የድርጅቱን ገቢ ሊያሳድጉ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ አማራጮችን በመጠቀም ገቢን ለማሳደግ አዲስ ስልት ነድፎ ለመሥራት በእንቅስቃሴ ላይ መሆኑን እና አላስፈላጊ ወጪዎችን ከመቀነስና ከመቆጣጠር አንፃር እምርታ መመዝገብ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ከተለያዩ ባንኮችና የክፍያ ድርጅቶች ጋር በጥምረት በመስራት የታዩ ይቴክኖሎጂ አጠቃቀምን የማሳደግ እና ዲጂታል የክፍያ አገልግሎት ስርዓት መፍጠር  መቻሉም ከታዩት ተጨባጭ ውጤቶች አንዱ መሆኑ ተጠቅሷል።

በሪፖርቱ ላይ እንደተገለጸው የሰራተኞችን የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና አጠቃቀም ክህሎት በማሳደግ እንዲሁም ኩባንያው ለደንበኞቹ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ቴክኖሎጂ መራሽ እንዲሆን በማድረግ በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ የሚገኘው የፐርፐዝብላክ ቴክኖሎጂ ክፍልም የኩባንያውን አይቲ ሲስተም ደህንነት የሚያረጋግጡ ተግባራትን በማከናወን የኩባንያውን ውስጣዊ አሰራር ለማቀላጠፍ አስችሏል።

ለተለያዩ ክልሎች ባቀረባቸው የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች  መሰረት በኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ አማራ፣ አፋር እና ጋምቤላ ክልሎች ከሚገኙ የእርሻ ልማት ድርጅቶች ጋር በጥምረት በመስራት 1,707 ሄክታር በማልማት ላይ የሚገኘው የፐርፐዝብላክ ግብርና ክፍል እንዲሁም የዳቦ ውጤቶችን ጨምሮ ልዩ ልዩ የባልትና ምርቶችን ለገበያ እያቀረበ የሚገኘው የኩባንያው ማቀነባበሪያ ክፍል ያሳዩት ውጤት የሚበረታታ መሆኑም ተገልጿል።

በመጨረሻም  በኩባንያው አጠቃላይ አፈጻጸም ላይ የነበሩትን ውስንነቶች በመቅረፍ እና ለተሻለ ውጤት መፍትሔ የሚሹ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የኩባንያው የሁብት ምንጮችን ማስፋት፣ የእቅድ  ዝግጅት እና የሪፖርት አቀራረብ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል የተባለ ሲሆን ይህንንም ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ የድርጅቱን የቢዝነስ አማራጮች እና አቅም ማሳደግ ያስፈልጋልም ተብሏል።

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከሳንቲም ፔይ የክፍያ አገልግሎት ሰጪ ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ።

የዕለት ተዕለት የደንበኛ አገልግሎቱን በማጠናከር እና በማሻሻል በሃገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ የኢኮሜርስ ግብይት ከዋኞች ውስጥ ተመራጭ ለመሆን እየሠራ የሚገኘው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሳንቲም ፔይ ከተሰኘ የክፍያ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙን የከገበሬው ኢኮሜርስ ዳይሬክተር አቶ አማኑኤል መለሰ አስታውቀዋል።

በመላው ዓለም ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን ዲጂታል የገንዘብ ኖቶችን እና ሳንቲሞችን የሚጠቀም ማኅበረሰብ የመፍጠር እንቅስቃሴን ተከትሎ ክፍያዎች ሁሉ በኦንላይን እና የመተግበሪያ አማራጮች እየተከናወኑ እንደሚገኙ ያነሡት ኃላፊው ፐርፐዝ ብላክ ኢትዮጵያ ይህንን የዘመናዊነት እንቅስቃሴ በመቀላቀልና የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት የኩባንያውን  ምርትና አገልግሎቶች ከሚጠቀሙ ግለሰቦች፣ የግልና የመንግሥት ተቋማት ከሚቀበላቸው የጥሬ ብር ክፍያዎች በተጨማሪ በገበሬው ኢኮሜርስ አማካኝነት ከተለያዩ የክፍያ አማራጮች ጋር በጥምረት እንደሚሠራ ገልጸዋል። ከዚህ ቀደም ቴሌብር፣ ፓይፓል ፣ የኔ ፔይ እና ሌሎችንም በመጠቀም መክፈል የሚቻልበትን መንገድ ለደንበኞች በማመቻቸት ሲሰራ የቆየ ሲሆን አሁን ደግሞ ከነዚህ በተለየ አገልግሎቱን ያቀላጥፋል ካለው ሳንቲም ፔይ ጋር በጥምረት መስራት  መጀመሩ ይፋ ሆኗል።




> "ከሌሎቹ የክፍያ አማራጮች በተለየ የሳንቲም ፔይ ደንበኞች ምንም አይነት ቅድሚያ ተቀማጭ ገንዘብ በሳንቲም ፔይ አካውንት ማስቀመጥ አይጠበቅባቸውም እንዲሁም የሁሉንም ባንኮች አካውንት በአንዴ ማንቀሳቀስ ያስችላቸዋል" ያሉት ሃላፊው "ድርጅቱ ከፐርፐዝብላክ ጋር ለመስራት የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚጠበቅበትን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት፤ ፐርፐዝ ብላክም አገልግሎቱን ለደንበኞቹ በሰፋት የማስተዋወቅ ስራዎች በቀጣይ የሚሰሩ ሲሆን በዋናነት ሁለቱም ድርጅቶች ደንበኞች ያሻቸውን በእጅ ስልካቸው መርጠው በሚያዘበት ፍጥነት ክፍያቸውን በመፈጸም የግብይት ሥርዓቱን ይበልጥ ቀልጣፋ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል ብለዋል።

ይህንንም የትእዛዞችን ደህንነት ጠብቆ በተመጣጣኝ ዋጋ በጊዜው ማድረስ፣ ቀሪ የክፍያ ገንዘብን ከገዢዎች በአግባቡ ሰብስቦ ለኩባንያው ማስረከብ እንዲሁም ያለገደብ በሃገሪአቀፍና አለምአቀፍ ደረጃ ተደራሽ የመሆን መሰረታዊ መመዘኛዎች መሰረት አድርገው ወደስራ ከሚገቡ የማድረሻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ጋር በማጣመር የከገበሬውን ምርትና አገልግሎቶች በላቀ ጥራት በመላው አለም ለማድረስ ይቻላል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የኢ-ኮሜርስ **kegeberw.com** ን በማስተዋወቅ ምርትና አገልግሎት አቅራቢዎች ከአምራቾች ጋር በአንድ ቦታ የሚገናኙበት እና የሚገበያዩበት በበይነ መረብ የግብይት ሥርዓት ከመዘርጋቱ ባሻገር 9858 ላይ በመደወል በተደረጉ ግብይቶች ባለፉት ዘጠኝ ወራት ብቻ 9,093,111.55- ብር ሽያጭ አከናውኗል፡፡

አክለውም "አሁን ይሸምቱ በኋላ ይክፈሉ" በማለት የከገበሬው ደንበኞች  በዱቤ አገልግሎት የኩባንያውን ምርትና አገልግሎቶች እንዲጠቀሙ የሚያስችል የአከፋፈል ስርአት በመዘርጋት ላይ ነን ያሉት ሃላፊው ይህም ደንበኞችን ይበልጥ ተጠቃሚ በማድረግ ደንበኞች የፐርፐዝብላክን ምርቶች እንዲጠቀሙ ይጋብዛል ሲሉም "ፈጣን የደንበኞች የዱቤ አገልግሎት" ስለተሰኘው የከገበሬው ቀጣይ እቅድ አስረድተዋል።

ይህም ኩባንያው በመላው ሃገሪቱ ከሚገኙ አምራችና ሸማቾች እንዲሁም የንግድ ተቋማት ጋር የሚኖረውን የአከፋፈል ስርአት ቀላል እና ፈጣን ያደርገዋል፣ ሃገር በቀል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችንም የሚያበረታታ ሲሆን ሳንቲምፔይን ለተለያዩ በማገናኘት የሃገር ውስጥ ምርቶችን ለማስተዋወቅ እና እንዲጠቀሙ ለማድረግ በእጅጉ ይረዳል። እንደሁሉም የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤትም የተገልጋዩን ጊዜና ጉልበትን በመቆጠብ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ነው ያሉት ዳይሬክተሩ።

በቀጣይም ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የራሱን ከገበሬው የክፍያ መተግበሪያ ለማበልጸግ በእቅድ መያዙን በማስታወቅ ከሌሎች ጋር በጥምረት ከሚሰራው በተሻለ ጥራት ተደራሽ ይሆናል ብለዋል።

## የከገበሬው የተቀናጀ ማስፋፊያ መርሃግብር በ 9 ወራት የእቅድ አፈጻጸሙ አበረታች ውጤቶችን አስመዝግቧል ተባለ።

የኩባንያውን የገበሬዎችን ህይወት የማሻሻል ውጥን እውን ለማድረግ በገጠራማው የሃገሪቱ ክፍል የሚገኙ አርሶ አደሮች ላይ ትኩረቱን በማድረግ የሚሰራው የከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሃግብር ገበሬዎችን በኩታ ገጠም እርሻ በማደራጀት፤ የግብርና ምክር አገልግሎት በመስጠት፤ የግብርና ግብዓት፣ የማይክሮ ፋይናንስ እንዲሁም የሜካናይዜሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል በመላ ሃገሪቱ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

የግብርና ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ ድርጅቱም ሆነ አርሶ አደሩ ከሚያገኘው ትርፍ ባሻገር የሸማች ገበያውን ዋጋ በማረጋጋት ረገድ የሚኖረው ሚና ቀላል አይደለም ያሉት ሃላፊው በክርቡም በይፋ ስራ በጀመሩ 5 ክላስተሮች የተለያዩ የአህል ዘሮች እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬዎችን በተሻለ ጥራትና ዋጋ አምርቶ ለገበያ እንደሚያቀርም ገልጸዋል።

KIEP
KEGEBEREW INTEGRATED EXPANSION PROGRAM

“

**በከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሃ ግብር ከሚተገበሩ ስራዎች መካከል ለገበሬዎችን የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አንዱ ሲሆን አርሶ አደሮች የኩባንያውን አክሲዮኖች በመግዛት ባለቤት እንዲሆኑ የማስቻልና በክላስተር በማደራጀት የዘመናዊ ግብርና ተጠቃሚ የማድረግ ሰፊ ስራዎች መሰራታቸው ተጠቁሟል።**

በዚህም ለ 54,159 ገበሬዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መሰጠታቸው የተገለጸ ሲሆን ከአርሶ አደሮች በተጨማሪ ለተለያዩ የመንግስት እና መንግስታዊ ላልሆኑ መ/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጥ መድረኮች ማዘጋጀቱንም አስታውሰዋል።

የፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ትሬዲንግ አክሲዮን ማኅበር ባቀረበው የ 2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ መርሃ ግብሩ 11 የክልል የተቀናጀ ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ቢሮዎችን ለማደራጀት በታቀደው መሰረት 64 በመቶ በሆነ አፈጻጸም በ 7 ክልሎች ቢሮዎችን ወደስራ ማስገባት መቻሉ የተጠቀሰ ሲሆን በተለያዩ 11 ከተሞችም ቅርንጫፍ ቢሮዎች ተከፍተዋል።

በተጨማሪም ለክራስተሮች ማስፋፊያ 187 ወረዳዎች በመምረጥ የቅርንጫፍ እና የወረዳ ኤክቴንሽን ማናጀሮችን ቀጥሮ በመሰራት ላይ ይገኛል።

በተደራጁ 43 የገበሬዎች ኩታ ገጠም እርሻዎችም የተለያዩ አትክልት ፍራፍሬዎች ለማምረት እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን የገለጹት አቶ አስናቀ ለነዚህም ገበሬዎች በተሸጡ የፐርፐዝብላክ አክሲዮኖች 5,991,845 ብር መሰብሰብ መቻሉን አስታውቀዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከገበሬው ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የእንስሳት መኖን ጨምሮ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት በመስጠት ትልቁ የግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅት ለመሆን የተሻሉ አማራጮችን እንደሚጠቀም በማስታወስ በቀጣይም የድርጅቱን በሀገሪቱ ትልቁ የኩታ ገጠም እርሻ አስተዳደር ኩባንያ የመመስረት አላማ እውን ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል ነው ብለዋል ሃላፊው።

ዋና አዘጋጅ፦ ሰላማዊት ደበበ
ሲንየር ሪፖርተር፦ ጌታባለው ገ/ሐና
ሪፖርተር፦ ኤደን ደነቀ

**ለበለጠ መረጃ**

ሰንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ
+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222
7151
www.purposeblackethiopia.com